ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
አዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕ/ማ/ቅ/ጽ/ቤት
EHTIOPIAN REVENUE AND CUSTOMS AUTHORITY
A.A. EXPORT AND OTHERS GOODS FACILITATION

ቀን 09/11/2004 ዓ.ም

- ለ፡ ጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
- ከ፡ ም/ስራ አስኪያጅ
  አ.አ. የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት

አበበ አስቻለው ኢድሚኩ
የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት
ምክትል አስኪያጅ

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በ03/5/04 በቁጥር ታ/ከ/ቀ/5/604 እና ጥር 7 ቀን 1996 በቁጥር አቤ/16/28/66 የተላለፈ መመሪያ በአሜሪካ መንግስት እርዳታ ሊሚካናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ወይም ከአሜሪካ አለም ዐቀፍ የልማት ኤጀንሲ ስራ ማስፈፀሚያ ወደ ሃገር የሚገቡና እና ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ ፍቅዷል።

ለዚህም ማስፈፀሚያ ጥር 7 ቀን 1996 በቁጥር አ.ወ 3/16/28/68 በተፃፈ የሽኝ ደብዳቤ የተላከውን መመሪያ 7 ገፅ እንዲሁም ከጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ዳይሮክቶሬት ዳይሮክተር የተላከ 4 ገፅ ቅፅ በድምሩ 11 ገፅ በዚህ ደብዳቤ ሽኝነት የተላከ ሲሆን በተላከው መመሪያና ቅፅ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን እየገለፅኩኝ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይበተኑ እ.አ.አ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የቆዩ ሠነዶች በተላላፈው መመሪያና ቅፅ መሰረት እየተጣራ እንዲበትን አሳስባለሁ።

ከበሬታ ጋር

ግልባጭ፡

- ለድሕረ ዕቃ አወጣጥ አዲት የሥራ ሂደት
- ለደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት
  አ.አ. የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሜሪካ የዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት
  አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

ለአዲስ አበባ የወጪ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

ቁጥር Ref. No. 650/36/2

ቀን Date 19 መጋቢት 2004

የግንዝብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በ3/5/04 በቁጥር ታ/ኪ/ቀ/5/604 በዓፈው ደብዳቤ በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግስት መካከል.ኢ.ኤ.አ ኖቬምበር 15 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው የቴክኒክ ትብብር ስምምነት አንቀጽ 8 (1) (a) እንደተመለከተው በአሜሪካ መንግስት እርዳታ ሰሚከናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ወይም ለአሜሪካ የለሰም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ ስራ ማስፈፀሚያ ወደ አገር የሚገቡ እና በአገር ውስጥ የሚገዙ እቃዎች ከማንኛውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የፈቀደ ሲሆን ይህን ለማስፈፀም ጥር 7 ቀን 1996 በቁጥር አመ3/16/28/66 በተፃፈ የሽኝ ደብዳቤ መሰረት መመሪያ ፑተሳሽ በሚሆኑ ከ2009 ጀምሮ ለሚያስገባቸው እቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ እንዲደረግ በማለት አስታውቋል።

ስለዚህ ከላይ የተፃፈውን ደብዳቤ እና ጥር 7 ቀን 1996 በቁጥር አቤ3/16/28/66 የተሰለፈው መመሪያ በአጠቃላይ 6 (ስድስት) ገጽ አያይዘን እየላክን በተሰለፈው ደብዳቤና መመሪያ መሰረት አስፈላጊው እንዲፈፀም እንገልፃለን።

- ለቀጥታ ዲሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕጋ ማስከበር ስራዎች ዘርፍ
- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ቡድን

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

- ለገንዝብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
- ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

tel. 011 662 99 00
011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሳ.ቁ. / P.O.Box

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቀን Date 08/12/2004

ቁጥር No. ፫፻፲፭/፻፭

ለ To

ጉዳዩ

የUSAID ኢትዮጵያ HIV/AIDS አመክሮአዊ ስርጭት ቅነሳ ፕሮጀክት ከመንግስት ጋር ስምምነት ለመፈፀም ስለመፍቀድ

የUSAID ኢትዮጵያ HIV/AIDS አመክሮአዊ ስርጭት ቅነሳ ፕሮጀክት ከመንግስት ጋር ስምምነት ለመፈፀም ስለመፍቀድ በተመለከተ ከUSAID Ethiopia ከተላከልን ደብዳቤ ጋር በተያያዘ ከ2005 ዓ.ም እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ የሚተገበረው የH

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Development

ቁጥር Ref.No

ቀን Date

ለገቢዎች ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል ኢ.ኤ.ስ. ኖቬምበር 15/1993 የተፈረመው የኤኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት በአሜሪካ መንግሥት አርዳታ ለሚከናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እንዲሁም ለአሜሪካ የዓለምዐቀፍ የልማት ኤጀንሲ ሥራ ማስፈፀሚያ ወደአገር የሚገቡ እና በአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የሚፈቅድ ሲሆን፣ ይህንኑ ስምምነት ፓርላማው አፅድቆታል።

ስለዚህ በስምምነቱ በተገባው ግዴታ መሠረት መፈፀም የሚያስችል መመሪያና ቅፅ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ፣ በናሙናው መሠረት ተከታታይ ቁጥር ያለው ቅፅ ትዘጋጅሎ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

ኑሩዲን አህመድ
ሚኒስትር

ስ.ሣ.ቁ 55 24 00, 55 28 00, 55 00 81,83,86,89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905, 1037
ፋክስ Fax 251-1-55 13 55, 55 14 96, 251-1-55 33 44
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa-Ethiopia

በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት ወደአገር የሚገቡና ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ስለሚሆኑበት አፈፃፀም

የወጣ መመሪያ

በኢትዮጵያና በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ መንግሥታት መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 15 ቀን 1993 ዓ.ም. የኤኮኖሚና የቴክኒክ ትብብር ስምምነት የተፈረመ በመሆኑ፣

የዚህ ስምምነት አንቀጽ 8 የአሜሪካ መንግሥት እና ሠራተኞቹ ወይም በሁለቱ መንግሥታት መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት በአሜሪካ መንግሥት እርዳታ ለሚከናወኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ወይም ለአሜሪካ የዓለምዐቀፍ የልማት ኤጀንሲ ሥራ ማስፈፀሚያ ወደአገር የሚገቡ እና በአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከማናቸውም ቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ የሚፈቅድ ስለሆነ፣

በስምምነቱ ከተቋቋመው የቀረጥና ታክስ ነፃ የመሆን መብት ውስጥ በአሜሪካ መንግሥት እርዳታ ለሚከሔዱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ወደአገር የሚገቡና በአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚሆኑበትን አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ከዚህ የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል፡-

1. <u>አውጪው ባለሥልጣን</u>

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ስምምነቱን ለማፅደቅ በወጣው አዋጅ ቁጥር 93 / 1986 መሠረት ይህንመመሪያ አውጥቷል።

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

2. የአሜሪካ ዓለምዐቀፍ ፣ልማት ድርጅት በቅፁ ላይ የጠዘረዘሩት ዕቃዎች ከአሜሪካ መንግሥት በተገኘ እርዳታ የተገዙ መሆኑን ያረጋግጣል።

3. የጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ዕቃዎቹ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቅዳል።

4. የጉምሩክ የመቅረጫ ጣቢያ በቅፁ ላይ የተዘረዘሩት ዕቃዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቅዳል።

5. <u>ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች</u>

በኢትዮጵያና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል በተፈረመው ስምምነት መሠረት ከአሜሪካ መንግሥት በተገኘ እርዳታ ለሚካሔዱ ፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ከአገር ውስጥ የሚገዙ ዕቃዎች ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ሲሆኑ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ይሆናል።

ሀ. ፕሮጀክት አስፈፃሚው አካል ከአገር ውስጥ የሚገዛቸውን ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ዓይነት ለዚሁ ዓላማ በተዘጋጀ ቅጽ ላይ ሞልቶ ለአሜሪካ ዓለምዐቀፍ ፣ልማት ድርጅት ያቀርባል።

2. የአሜሪካ ዓለምዐቀፍ ፣ልማት ድርጅት በቅፁ ላይ የተዘረዘሩት ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከአሜሪካ መንግሥት በተገኘ እርዳታ የተገዙ መሆኑን ያረጋግጣል።

3. የፈዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ዕቃዎቹና አገልግሎቶቹ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገዙ ይፈቅዳል።

4. ፕሮጄክት አስፈፃሚው ቅድን ለዕቃው ወይም ለአገልግሎቱ አቅራቢ በማስረከብ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ ሆኖ ግዥውን ይፈፅማል።

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

6. የቅፅ ዝግጅት

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው ወደሕገር ሰሚገቡት ዕቃዎች የሚያገለግል ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ ሆኖ በተዘጋጀው ናሙና መሠረት ተገቢውን ቅጽ ይጠቀማል።

2. ቅፁ በአራት ኮፒ የሚዘጋጅ ሆኖ እንደአግባብነቱ ለጉምሩክ ወይም ለፈዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን፣ ለአሜሪካ ዓለምዐቀፍ የልማት ድርጅት፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ለተመዘገበው ሻጭ፣ ለትራንዚሪ መምሪያ እንዲደርስ ይደረጋል።

7. ስለማስታወቅ

በአሜሪካ መንግሥት እርዳታ ተገዝቶው ወደአገር በገቡ ዕቃዎች እና ከአገር ውስጥ በተገዙ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ ሊከፈል ሲገባ ነፃ የተደረገውን ቀረጥና ታክስ እንደአግባቡነቱ ጉምሩክ፣ ገቢ ባለሥልጣን ወይም [illegible] ለገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ለገቢዎች ሚኒስቴር ሪፖርት ያደርጋሉ።

8. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከጥር 15 ቀን 1996 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር 5/1996

ሱፍያን አህመድ
ሚኒስትር

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስትር

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

3069
ግ/ሥ

ቁጥር 6ሆ·01182/2
Ref. No.
ቀን 03 ሐምሌ 2004
Date

ለአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በ 07/05/96 በቁጥር አመ3/16/28/66 ያስተላለፈው መመሪያ ለአፈፃፀም መላካችን ይታወሳል። በመመሪያ አንቀጽ 4/3 የጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ዕቃዎቹ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ይፈቀዳል ይላል። ሆኖም የባለሥልጣኑ ዋና መ/ቤት የቀረጥ ነፃ መፍቀድ ሥራ ለቅ/ጽ/ቤታችሁ የተላለፈ በመሆኑ በዚሁ መሠረት እንዲስተናገዱ እንዲደረግ እያስታወቅን ሁለት /2/ ገጽ ፎርም አባሪ ተደርጉ የተላከ መሆኑን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

ሲሳይ አስረስ
የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues and Customs Authority

ግልባጭ፣

- ለቅ/ጽ/ቤቶች ማስተባበሪያ ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትልና ድጋፍ ቡድን

ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣

የአ.አ. የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት
የሬጅስትና ሚዛ ቡድን
የደረሰበት ቀን 04/11/04
የተቀባይ ፊርማ
የተመራበት ክፍል ለመንግስት የተሰጠ
የመራው ኃላፊ ፊርማ
የተመራበት ቀን 04/11/04
የገቢው ዝርዝር ቁጥር 13/0850
የተመዘገበበት ቀን

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!